የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ—ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 3
ADDIS ABABA–28th October, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፫/፲፱፻፺፮ ዓ.ም.
በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ የተፈረመውን ስምምነት እና ፕሮቶኮሉን ለመቀበል የወጣ አዋጅ .................. ገጽ ፪ሺ፬፻፳፬

## CONTENTS

Proclamation No. 373/2003
The convention for the protection of Cultural Property in the event of Armed Conflict and its first protocol Accession Proclamation .............................. Page 2424

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፫/፲፱፻፺፮

## በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ የተደረገውን ስምምነት እና ፕሮቶኮሉን ለመቀበል የወጣ አዋጅ

በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፮ በሄግ የተደረገውን ስምምነት በኢትዮጵያ መቀበል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህ ስምምነትና ፕሮቶኮል የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶችን ለመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረው በመሆኑ፣

ይህንን ስምምነትና የመጀመሪያ ፕሮቶኮል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የተቀበለው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ—መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ የተፈረመውን ስምምነት እና ፕሮቶኮሉን ለመቀበል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፫/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## *PROCLAMATION NO. 373/2003*

## *A PROCLAMATION TO ACCEDE THE CONVENTION FOR THE PROTECTION OF CULTURAL PROPERTY IN THE EVENT OF ARMED CONFLICT AND ITS FIRST PROTOCOL*

WHEREAS, it is found essential that Ethiopia Accede the convention for the Protection of Cultural Property in the Event of Armed Conflict Signed at Hague on the 14 day of May 1954;

WHEREAS, the said convention and protocol is found to be paramount importance in protecting the Ethiopian Cultural Heritage;

WHEREAS, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has Accede said convention and its first protocol at its session held on the 28th day of October, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as ''The convention for the Protection of Cultural Property in the event of Armed Conflict and its first protocol Accession Proclamation No. 373/2003''.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ስምምነቱን ስለመቀበል</u>

እ·ኤ·አ· ሜይ ፲፬ ቀን ፲፱፻፶፬ በጦርነት ጊዜ ቅርሶችን ለመጠበቅ በሄግ የተፈረመው ስምምነትና የመጀመሪያው ፕሮቶኮሉ ተቀባይነት አግኝቷል።

፫· <u>የኢትዮጵያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከኅብረተሰቡ ጋር በመተባበር ስምምነቱን በሥራ ላይ የማዋልና አፈጻጸሙንም የመከታተል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. *Accession of convention*

The Convention for the protection of Cultural property in the event of armed conflict and its first protocol Signed at Hague on the 14th day of May 1954 is Acceded.

3. *Powers and Responsibility of Authority for Research & conservation of Cultural Heritage (ARCCH)*

The Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage is hereby empowered to undertake all acts necessary of the implementation of the Convention and its first protocol in co-operation with concerned Federal and Regional Government organs, Non-Governmental organizations as well as with Communities.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 28th day of October, 2003.

Done at Addis Ababa, this 28th day of October, 2003

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE